የአፖልናርዮስ ደቀ መዝሙር የሆነው የመናፍቁ ዘበነ ለማ ስሕተቶች - ክፍል አንድ

አፖልናርዮስ ከመቅዶንዩስ ጋር አብሮ የተወገዘ ሰው ነው። መቅዶንዮስ የተወገዘው መንፈስ ቅዱስን ፍጡር በማለቱ ሲሆን አፖልናርዮስ ደግሞ ኢየሱስ ፍጹም አምላክ (መለኮት) ብቻ ነው በሚለው ትምህርት ነበር። እንደ እርሱ ትምህርት ከሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ፍጹም አምላክ (መለኮት) ብቻ ነው፣ ፍጡር አይደለም። ሰው ሆነ ብንልማ ሰው የሆነ ሁሉ ጎጢአት ስለሚሠራ ጎጢአት ሠራ ልንለው ነው። ስለዚህ ቃል የተዋሐደው ከእግዚአብሔር ከተገኘችው ሕያዊት ነፍስ ጋር እንጂ፣ ከሥጋዊና ከደማዊ አካል ጋር አይደለም (‹‹የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ከዓለም እስከ ኢትዮጵያ በዲያቆን ብርሃኑ አበጋዝ ገጽ 121)።

እርግጥ ነው እርሱ እንዳለው ክርስቶስ ፍጡር አይደለም። ይህ ማለት ግን ፍጹም ሰው አይደለም ማለት አይደለም። ለአፖልናርዮስ ምክንያት የሆነው አርዮስ ኢየሱስ አምላክ አይደለም የሚለው የስሕተት ትምህርት ነው። ለእርሱ ምላሽ እሰጣለሁ ብሎ እርሱም ሌላ ስሕተት ውስጥ ገባ እንጂ።

የክርስቶስን መካከለኝነት (አማላጅነት) ለመቃወም ሲል ስሕተት ውስጥ የገባው ዘበነ ለማም እንደ ግብር አባቱ እንደ አፖልናርዮስ ኢየሱስ አምላክ ብቻ መሆኑን አጉልቶ እያሳየ በለዘብታ ፍጹም ሰው መሆኑን ግን በመካድ ላይ ይገኛል። ከዚህ በፊት በሲዲ ያሰራጫቸው ሦስት የስሕተት ትምህርቶች ኪዳነ ምህረት በተሰኙ ቡክሌቶች በሦስት እትም ማለትም በቁጥር 10፣ 11 እና 22 ላይ ምላሽ መሰጠቱ ይታወሳል።

በዚህ ጽሑፍ ክርስቶስ ፍጹም ሰው መሆኑን እንዴት እንደሚሸፍን ለማሳየት ተሞክሯል። አንባቢ በቀላሉ ሐሳቡን እንዲከተል በመጀመሪያ የዘበነ ጽሑፍ ይሰፍርና በመቀጠል የስሕተት ሐሳቡ ይቀመጣል።

‹‹የመናፍቃን ታላቁና መሠረታዊው ስሕተታቸው ወልድ ኢየሱስ ክርስቶስን ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ነጥለውና ገንጥለው ማየታቸው እንደ ሆነ ገልፀናል አሁንም ወልድ አማላጅ ነው ለማለታቸው መሠረቱ ይህ አስተሳሰባቸው ነው። እዚህ ላይ ሁለት መሠረታዊ ነገሮችን እንይዛለን 1. አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ በመፍጠር፣ በመግዛት፣ በሥልጣን፣ በማድረግና ባለ ማድረግ ፍፁም አንድ ናቸው ብሎ ማመን 2. የመለኮትና የትስብዕትን ፍፁም ተዋሕዶ ማመን።... እነሱ የሚያምኑት ወልድን አማላጅ (ለምኖ የሚያሰጥ) መሆኑን ሲሆን አብና መንፈስ ቅዱስ ግን የሚሰጡ እንጂ የማይለምኑ መሆናቸውን ነው ይህም ማለት ወልድ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ተለይቶ ይለምናል ብለው ያምናሉ ማለት ነው ይህ ሆነ ማለት ደግሞ ማንም ህሊና ያለው ቢመዝነው ወልድ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ያንሣል እንደ ማለት ይቁጠራል ሎቱ ስብሐት። ሦስቱም አንድ መሆናቸውን የሚያምን ማንም ቢኖር ሁለት አማራጭ ብቻ ነው ያለው፤ አንድም አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ሦስቱም ያማልዳሉ ማለት፣ ካልሆነም አብ ወልድ መንፈስ ቅዱስ ሦስቱም ይፈርዳሉ እንጂ አያማልዱም ብሎ ማመን። ከዚህ ውጪ እያመኑ ግን እኩል ናቸው ማለት አይቻልም››

በዚህ የዘበነ ጽሑፍ ውስጥ አፖልናርዮስ በግልጽ ይታያል። ምክንያቱም ኢየሱስ ፍጹም አምላክ መሆኑን ሲነግረን ፍጹም ሰው የመሆኑን የተዋሕዶ ምስጢር በደብዛዛው ነው ያነሣው። እሱ እንዳለው ኢየሱስ ክርስቶስ አምላክ ነው። ዘበነ ከዚህ ሐሳቡ ቀደም ብሎም እንዳሰፈረው መጽሐፍ ቅዱስ ይህን በተደጋጋሚ ያረጋግጣል። በእኛ እምነት የኢየሱስን አምላክነት የሚክድ ሰው ቢኖር ክርስቲያን ሊሰኝ አይገባውም። ሊነሣ የሚችለው ጥያቄ አምላክ ከሆነ እንዴት ነው አማላጅ የሚባለው? እሱ አምላክ ከሆነ ወደ ማን ነው የሚማልደው?

‹‹ክርስቶስ፤ ምንም እንኳ ዓለማትን የፈጠረና ሁሉ ከእርሱ በእርሱ ለእርሱ የሆነ ቢሆንም (ሮሜ 11÷36) ደኻ እንደ ነበር (ሉቃስ 9÷58)፣ ምንም እንኳ ፈዋሽ ቢሆንም (ማቴዎስ 4÷23) እንደ ታመመ (ኢሳይያስ

53÷3)፣ ምንም እንኳ ጻድቅ ቢሆንም (ኢሳይያስ 53÷11) ኀጢአት ሆነ እንደ ተባለ (2ኛ ቆሮንቶስ 5÷21)፣ ምንም እንኳ ድል አድራጊ ቢሆንም (ቄላስይስ 2÷15) እንደ ሞተ (1ኛ ቆሮንቶስ 15÷3)፣ ምንም እንኳ ጌታ ቢሆንም (ሮሜ 10÷9) ባሪያ እንደ ተባለ (ኢሳይያስ 53÷11) አያውቁ ይሆን? ስለዚህ እንደ ፍጹም አምላክነቱ ሁሉን የሚገዛ፣ በሁሉ ላይ ጌታ የሆነ፣ ለሁሉ የሚያስፈልጋቸውን የሚሰጥ በሁሉ ላይ የሚፈርድ ሲሆን እንደ ፍጹም ሰውነቱ ደግሞ በሰይጣን የተፈተነ፣ ዞሮ ያገለገለ፣ የጸለየ፣ እኛን ስለ ማዳን መከራ የተቀበለና የሞተ መሆኑን ማስታወስ ጠቃሚ ነው። ስለዚህ ወደ ማን ነው የሚያማልደው? ለሚለው ጥያቄ በዚህ ምድር በነበረ ሰዓት ሲጸለይ ወደ ነበረበት ነው የሚያማልደን የሚል ምላሽ ይሰጣል (ኢየሱስ እውነተኛ አማላጅ ጻድቅ ፈራጅ ገጽ 65)።

ይህን ነው እንግዲህ ዘበነ እየካደ እሱ የሚፈልገውን ብቻ ተቀበሉ የሚለው። ኢየሱስ አምላክ ነው አምላክ ነው የሚለውን የሚደጋግመው የምልጃውን ሥራ ለመቃወም መሆኑ ግልጽ ነው። የኢየሱስን ፍጹም ሰውነት ያልተጻፈ ያክል መሸፋፈን ነገረ ድነትን ከማድበስበስ አይተናነስም። ኢየሱስ ከአብና ከመንፈስ ቅዱስ ጋር እኩል ነው? አዎ!!! በምን? በአምላክነቱ!!! ግን ደግሞ መጽሐፍ ቅዱስ ከመላእክት ይልቅ በጥቂት አንሶ የነበረውን ኢየሱስን ያሳያናል (ዕብራውያን 2፡9)። ይህ ማለት በፍጹም ሰውነቱ መሆኑን ግልጽ ነው። ስለዚህ እኛ የክርስቶስ ደቀ መዛሙርት ኢየሱስ ያማልዳል ስንል አምላክነቱን ክደን ሳይሆን በፍጹም ሰውነቱ የሠራልንን ሥራ አሜን! ብለን ተቀብለን ነው።

“ክርስቶስ በመለኮት ሕያው ሲሆን ስለ እኛ በሥጋ እንደታመመ በሥጋም እንደ ሞተ እንናገራለን መለኮት በተዋሐደው ሥጋ ታመመ ግን ከሕማም ወገን መለኮትን ምንም ምን ከቶ አገኘው አንልም ይህ አይሆንም መለኮት በሥጋ ሕማማትን እንደ ተቀበለ እንናገራለን እንጂ” (ሃይማኖተ አበው ምዕራፍ 82 ክፍል 2 ቊጥር 38)።

‹‹እንደዚህም ወንጌላዊ ዮሐንስ እኛ ለአባቱ አንድ እንደ ሆነ ልጅ ክብር ያለ ክብሩን አየነ አለ፤ <u>በሥጋ ባሕርይ ግን ሰው ይባላል መሥዋዕትነትን፣ አስታራቂነትን እውነትን ገንዘብን ያደረገ እንደ ሆነ</u> ስለ እርሱ ዮሐንስ እንደተናገረ ታወቀ (ሃይማኖተ አበው ምዕራፍ 35 ክፍል 1 ቊጥር 7)።

ከዚህም ሌላ የክርስቶስን መካከለኝነት ከእርሱ ነጥቆ ለፍጡራን ለመስጠት መሞከሩም ደግሞ መታየት ያለበት ነጥብ ነው። ከዚያ በፊት ግን ከክርስቶስ ጋር በተያያዘ ያሰፈረውን እነሆ፤

በዘበነ ትምህርት መሠረት አማላጅ ለምኖ ያሰጣል እንጂ ሰጪ አይደለም ኢየሱስ ክርስቶስ ግን የሚሰጥ እንጂ የሚያሰጥ ስላልሆነ አማላጅ አንለውም… እንግዲህ ሁሉ በእርሱ የሚሆን ከሆነ ከማን ምን ይለምን? የሁሉ አስገኝና ፈጣሪ እርሱ ከሆነ ማድረግ እንጂ መጠየቅ ስለምን ያስፈልገዋል?››።

ዘበነን ለዚህ ስሕተት የዳረገው አማላጅ ለሚለው ቃል ያለው ጭፍን ጥላቻ እና ትርጓሜውን አለማወቅ ነው … ላከውም፣ አማለደም አስታረቀም ቢባል ከአባቱ በመለኮቱ በምንም አያንሥም። ለዚህም የባህላችንን ምሳሌ እንመልከት፤ በቀድሞው ሥርዓት ሴት ልጅ የፈለገ ሰው ነገሩ እንዲከብድለት ደጃዝማች ወደ ደጃዝማች ወይም ፊታውራሪ ይልካል፤ ደጃዝማች ሄደው ይለምናሉ። በዚህም የለማኙ ያማላጁ የደጃዝማች ማዕረግ ከሚሾሙት ከፊታውራሪ አያንሥም። ማስታረቅም ማማለድም ክብር አይቀንስም፣ ማዕረግ አያዋርድም (‹‹ሁሉም ሁሉን

ይወቅ ገጽ 48። ኢየሱስ እውነተኛ አማላጅ ጻድቅ ፈራጅ ገጽ 12)።

ዘበነ ሊነግረን እየሞከረ ያለው ኢየሱስ የሚለምን አይደለም፤ እርሱ ራሱ የሚለመን እንጂ የሚለውን ነው። ነገር ግን እርሱ እንደ ቅዱስ የሚመለከተው በ2000 የታተመው ሰማንያ አሐዱ እኔ ስለ እነርሱ እለምናለሁ፤ የምለምንህ ስለ ዓለም አይደለም፤ ስለ ሰጠኸኝ ነው እንጂ፤ ያንተ ናቸውና በማለት ያስቀመጠውን አልቀበልም ማለቱ ይሆን (ዮሐንስ 17፡9)? ከዚህም ሌላ ከወደዳችሁኝስ ትእዛዜን ጠብቁ። እኔም አብን እለምነዋለሁ፤ እርሱም ለዘለዓለም ከእናንተ ጋር ይኖር ዘንድ ሌላ አጽናኝ ይልክላችኋል (ዮሐንስ 14፡15-16) ተብሎም ተጽፏል። ዘበነ እንደሚለው እርሱ ራሱ አምላክ አይደለም እንዴ? ምን መለመን ያስፈልገዋል? እኔ እሰጣችኋለሁ ማለት ሲገባው ለምንድን ነው እኔ እለምናለሁ እርሱ ይሰጣችኋል ያለው? ዘበነ ለዚህ ጥያቄ ምን መልስ ይኖረው ይሆን? ምክንያቱም እርሱ የኢየሱስን አምላክነት ብቻ እንጂ ሰው የመሆኑን ነገር ትቶታልና።

ሌላው ዘበነ የኢየሱስን አማላጅነት ሸፍኖ ለፍጡራን የምልጃ ሥራ ለመስጠት ጥቅስ እስከ ማጣመም ድረስ የሄደው ርቀት ሊያሳይ የሚችል ሀሳብ እንዲህ አስፍሯል፤

‹‹በመጨረሻም እንደ ቤተ ክርስቲያናችን አስተምሮ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር ላይ የፈጸመው ነገር የማስታረቅ ስራ ይባላል ያንን የማስታረቅ ሥራ ግን አሁንም እየወደቀ እየተነሳ አይሰራውም ለቅዱሳኑ ሰጥቷቸዋልና። 2ኛ ቆሮ 5፡18-19 ነገር ግን የሆነው ሁሉ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን ከእግዚአብሔር ነው እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና በደላቸውን አይቆጥርባቸውም ነበር በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ። ሁላችን መጽሐፍ እርስ በእርሱ እንደማይጋጭ እናምናለን ይህ ከሆነ ቅዱስ ጳውሎስ በግልፅ ቋንቋ ያስታርቅ ነበርና በማለት ክርስቶስ በምድር ላይ የማስታረቅን ስራ እንደሰራ “ነበርና” በሚለው በአላፊ ወይም ፍፃሜውን ያገኘ ድርጊት መሆኑን በሚገልፅ ዘይቤ ካስረዳ በኋላ ይህ የመጽሐፍ ቅዱስ የአፃፃፍ ዘይቤ ነው እንዳንል የማስታረቅን አገልግሎት ከሰጠን እንዲሁም በእኛ የማስታረቅ ቃል አኖረ በማለት ከዚያ በኋላ የማስታረቁን ሥራ ለእነሱ ለቅዱሳኑ እንደሰጣቸው በማያሻማ ሁኔታ ገልፆልናል ዘበነ ይህን ሐሳብ ያሰፈረው በርግጥ ለቅዱሳን ቀንቶ ሳይሆን የጌታን ክብር ለመሸፈን በማሰብ መሆኑ ግልጽ ነው። ለመሆኑ ይህ የዘበነ ሐሳብ ምን ያህል መጽሐፍ ቅዱሳዊ ነው?

ዘበነ የጠቀሰው ጥቅስ ሙሉ ቃል ነገር ግን የሆነው ሁሉ፥ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን፥ ከእግዚአብሔር ነው፤ እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና፥ በደላቸውን አይቆጥርባቸውም ነበር፤ በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ። እንግዲህ እግዚአብሔር በእኛ እንደሚማልድ ስለ ክርስቶስ መልክተኞች ነን፤ ከእግዚአብሔር ጋር ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን የሚል ሲሆን (2ኛ ቆሮንቶስ 5፡18-20) እርሱ ግን ቁጥር 18 እና 19 ላይ ያለውን ብቻ ቆርጦ ነገር ግን የሆነው ሁሉ፥ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ካስታረቀን የማስታረቅም አገልግሎት ከሰጠን፥ ከእግዚአብሔር ነው፤ እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ ዓለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበርና፥ በደላቸውን አይቆጥርባቸውም ነበር፤ በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ የሚለውን ብቻ ነው ያስቀመጠው። ቁጥር ሃያን ያላካተተበት ምክንያት ሐዋርያው በእኛም የማስታረቅ ቃል አኖረ የሚለውን ግልጽ የሚያደርግበት ወይም ደግሞ የማስታረቅ ቃል ተብሎ የተገለጸው ምን እንደሆነ የሚያሳይበት በመሆኑ ነው።

ክፍሉ ዘበነ ለኑፋቄ ትምህርቱ እንደሚለው ያለ መልእክት አያስተላልፍም። ምንባቡ የሚናገረው እግዚአብሔር ሰዎችን ወደ ንስሐ እንዲጠሩ (እግዚአብሔርንና ሰዎችን ለማስታረቅ የሚሆነውን ወንጌል እንዲናገሩ) እንደላካቸው ነው። ይህን ሐሳብ ለማስረዳት ዘበነ በሚወደው በሰማንያ አሐዱ ላይ ሀሳቡ ምን ተብሎ እንደሰፈረ ማሳየቱ የተሻለ ሊሆን ይችላል ነገር ግን ሁሉ በክርስቶስ ከራሱ ጋር ከአስታረቀን፣ የማስታረቅ መልእክትንም (ይህን ቃል ልብ ይበሉ) ከሰጠን ክእግዚአብሔር ዘንድ ነው። ኀጢአታቸውን ይቅር ብሎ በደላቸውንም ሳያስብ

እግዚአብሔር በክርስቶስ ዓለሙን ከራሱ ጋር አስታርቋልና፤ የእርቅ ቃሉንም በእኛ አደረገ፤ የይቅርታውንም መልእክት ሰጠን (ይህን ቃል ልብ ይበሉ)። እኛስ በክርስቶስ አምሳል እንለምናል፤ እግዚአብሔርም በእኛ መጽናናትን ይሰጣችኋል፤ ከእግዚአብሔር ጋር ትታረቁ ዘንድ በክርስቶስ እንለምናችኋለን (ይህንም ልብ ይበሉ)››።

የመጽሐፉ ሐሳብ ይህ ከሆነ ዘበነና መሰሎቹ ጥቅሱን ያለ መልእክቱ ማናገር ለምን ፈለጉ? ቢባል የሚኖረው መልስ እነርሱ ቅዱሳን የሚሏቸው አካላት አማላጅ መሆናቸው የሚያስረዳ ጥቅስ ስለ ሌለ የሚል ይሆናል።

ዘበነ ክፍል አንድ ብሎ በለቀቀው ነፋቄ ውስጥ በዋናነት የረጫቸው ኑፋቄዎች እነዚህን ይመስላሉ። ክፍል ሁለት ብሎ የሚጽፈውን ደግሞ እንጠብቃለን!

ቴዎድሮስ ደመላሽ